**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት**
**የጸሀፊ (ክለርክስ) ቢሮዎች አሰራሮች ማስታወቂያ**
**በዲሰምበር 2021 የተሻሻለ**

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የጸሀፊ (ክለርክ'ስ) ቢሮዎች፣ ሰዎች ሰነዶች ፋይል እንዲያደርጉና መዝገቦችን በአካል እንዲመለከቱ በጁላይ 12፣ 2021 በአካል የሚደረጉ ስራዎች ጨምሯል። ኦሚክሮን በተባለ የኮቪድ አይነት ምክኒያት የጸሀፊ (ክለርክ'ስ) ቢሮዎች፣ ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ፣ በአካል በቢሮ የሚሰሩ ሰራተኞች ቁጥር ይቀንሳል። ሁሉም ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ቢሮዎች ከታች ካልተመለከተ በስተቀር ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5፡00 ፒ.ኤም. ክፍት ይሆናሉ። በርቀት የሚሃሄዱ አገልግሎቶችም (ሪሞት ሰርቪስስ) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ይገኛሉ። በቴሌፎን፣ ኢመይልና በቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) በመጠቀም ለጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጁ ሰራተኞች አሉን። በጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮዎች በአካልና በርቀት ስለሚከናወኑ ስራዎች በተመለከተ መረጃ ከታች ይገኛል።

ሰነዶችዎን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግ የማይችሉ ከሆነ በሞልትርየ የፍርድ ቤት ህንጻ 1ኛ ፎቅ (ፈረስት ፍሎር)፣ በህንጻ A እና ህንጻ B በሚገኘው የመረጃ ዳስ (ኢንፎርሜሽን ቡዝ) ቀጥሎ ባለው መጣያ ሳጥን (ድሮፕ ባክስ) ፋይል ስታምፕ አድርገው መጣል ይችላሉ፣ ወይም በየጸሀፊ (ክለርክ'ስ) ቢሮዎች ፋይል ማድረግ ይችላሉ። እባክዎን ሰነዶች ፋይል ሲያደርጉ የሁሉም አካላት የቴሌፎን ቁጥርና ኢመይል አድራሻ ያቅርቡ። አብዛኛዎቹ ችሎቶች (ሂሪንግስ) እና ሽምግልናዎች በርቀት ይካሄዳሉ። የፍርድ ቤት ችሎቶች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የዋና ዳኛ (ቺፍ ጃጅ) ጆሰ-ሀሪንግ ትእዛዝን በሚከተለው Order by Chief Judge Josey-Herring ይመልከቱ።

**ኤሌክትሮኒካዊ ክፍያዎች**

ሱፒርየር ፍርድ ቤት ለተወሰኑ የፍርድ ቤት ክፍያዎች፣ ቅጣቶችና ወጪዎች፣ በአካል እና ኤሌክትሮኒካዊ የክፍያ መግቢያችን (ፖርታል) በሆነው ፕሮምፕትፐይ (PromptPay) በመጠቀም ክፍያዎች በመቀበል ላይ ይገኛል። ደቢት ካርድ፣ ክሬዲት ካርድ (አመሪካን ኤክስፕረስ፣ ዲስካቨር፣ ማስተርካርድ፣ ቪዛ) ወይም ኤ.ሲ.ኤች. ኤሌክትሮኒካዊ ቼክ በመጠቀም ሊደረጉ ይችላሉ። ለያንዳንዱ ግብይት (ትራንዛክሽን) $1.00 የሚከፈል ሲሆን ደቢት ወይም ክሬዲት ካርድ መጠቀሚያ ተጨማሪ 2.5% ክፍያም ይከፍላሉ።

የሚከተሉትን ግብይቶች (ትራንዛክሽንስ) በፕሮምፕትፐይ መግቢያችን (PromptPay portal) በመጠቀም መክፈል ይችላሉ፡

- የቦንድ (የገንዘብ ዋስ) ክፍያዎች (ለወንጀለኛና የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍያዎች በክሬዲትና ደቢት ካርዶች የሚደረጉ ክፍያዎች)፣
- የመከላከያ ትእዛዝ (ፕሮቴክቲቭ ኦርደር) ክፍያዎች (ከ$1,000.00 በታች)፣
- ማእቀቦች (ሳንክሽንስ)፣
- ቅጣቶች፣
- የምዝገባና ኤስክሮ ክፍያዎች ጨምሮ ፍርድ ቤት ያዘዛቸው ክፍያዎች፣
- የተረጋገጡ ቅጂዎች (ሰርቲፋይድ ካፒስ)፣
- የመዝገብ ፍለጋ ጥያቄዎች (ሬከርድ ሰርች ሪክዌስትስ)፣
- የጋብቻ ማመልከቻዎች፣ የጉዲፈቻ አቤቱታዎች፣ የማህተም መስበሪያ ማመልከቻዎች (አፕሊኬሽንስ ቱ ብሬክ ሲል)፣ የታተሙ ጉዳይ አይነቶች የተመለከቱ ሰነዶች፣
- የቤት ውስጥ ብጥብጥ ጉዳዮች የይግባኝ ማስታወቂያዎችና ፍርድ ቤት ያዘዛቸው ክፍያዎች፣ እና
- ለተወሰኑ የኑዛዜ ማረጋገጫ ጉዳዮች ተጨማሪ ደብዳቤዎችና የፍርድ ቤት ወጪዎች

የኤሌክትሮኒካዊ ክፍያ መግቢያ (ፖርታል) ለመጠቀም የሂሳብ መጠየቂያ ደረሰኝ ይቀበላሉ። ክፍሎቹን (ዲቪዥንስ) እንደሚከተለው ያግኙዋቸው፡

| ክፍል (ዲቪዥን) | ቴሌፎን | ኢሜይል |
|---|---|---|
| የወንጀል ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን) | 202-879-1840 ወይም ለቅዳሜ የዋስ ክፍያ በተመለከተ ብቻ 202-879-4789 | **የዋስትና ክፍያዎች (ቦንድስ)**<br>BondPayPortal@dcsc.gov<br>**ቅጣቶች፣ ክፍያዎችና ካሳዎች**<br>CRMPay@dcsc.gov |
| የፍትሐብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)<br>- የፍትሐብሔር እርምጃዎች (ሲቪል አክሽንስ) ቅርንጫፍ<br>- የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ<br>- አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች (ስሞል ክለይምስ) ቅርንጫፍ | 202-879-1133<br>202-879-4879<br>202-879-1120 | CivilDocket@dcsc.gov<br>LandlordandTenantDocket@dcsc.gov<br>SmallClaimsDocket@dcsc.gov |
| የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን) | 202-879-0157 | **የሲ.ፒ.ኦ. ወይም ኤ.ኤስ.ኦ. ፍርድ ቤት ያዘዛቸው ክፍያዎች**<br>FamilyCourtCIC@DCSC.gov<br>**ዲ.ቪ.ኤም. ቦንድና ፍርድ ቤት ያዘዛቸው ክፍያዎች**<br>BondPayPortal@dcsc.gov |
| የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት) | 202-879-1212 | **የመዝገብ (ኬዝ) ክፍያዎች**<br>FamilyCourtCIC@dcsc.gov<br>**ቅጂዎች**<br>FamilyCourtCertifiedCopies@dcsc.gov<br>**ጋብቻ**<br>MarriageBureauReceipts@dcsc.gov<br>**የዋስትና ክፍያዎች (ቦንድስ)**<br>FamilyBonds@dcsc.gov |
| የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) | 202-879-9460 | ProbateInquiries@dcsc.gov |
| የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን) | 202-879-1737 | TaxDocket@dcsc.gov |

ለሁሉም ሌሎች ክፍያዎች በhttps://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በሚገኘው የኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ ኢ-ፋይሊንግ ሲስተማችን በመጠቀም መክፈል ይችላሉ።

ተደጋግመው ለሚጠየቁ ጥያቄዎች በተመለከተ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች ድረገጽን ይጎብኙ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/Payment-Portal-FAQs.pdf።

**ቅጂዎችና የተረጋገጡ ቅጂዎች (ካፒስ ኤንድ ሰርቲፋይድ ካፒስ)**

ቅጂዎችና የተረጋገጡ ቅጂዎች በሙሉ በሚመለከተው ክፍል (ዲቪዥን) ይሰጣሉ። እነዚህን ጥያቄዎች በአካልና በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማድረግ ይቻላል። ሰነዶችን ከያንዳንዱ ክፍል (ዲቪዥን) በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ከታች ያሉ መመርያዎች ይመልከቱ። የተረጋገጠ ቅጂን ኢሜይል በመጠቀም ሲጠይቁ እባክዎን ርእሰ ጉዳይ (ሳብጀክት ላይን) በሚለው "Request for Certified Document "የተረጋገጠ ቅጂ ጥየቃ"" ብለው ይጠቀሙ። ለሁሉም የቅጂ ጥያቄዎች በሚላከው ኢሜይል እየተጠየቀ ያለው ሰነድ ስም፣ የመዝገብ ቁጥር (ካለ)፣ የተከራካሪ አካላት ሙሉ ስም፣ እና የእርስዎ ስም፣ ቴሌፎን ቁጥርና ኢሜይል አድራሻ ያካትቱ።

**ሶስት ማህተሞች (ትሪፐል ሲልስ)**
የሶስት ማህተሞች (ትሪፐል ሲልስ) ጥያቄ በኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ ድረገጽ https://www.dccourts.gov/superior-court/e-filing በኩል መደረግ ይኖርበታል። ድረገጹ መጠቀም የማይችሉ ከሆነ የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) ዘንድ በመሄድ መጠየቅ ይችላሉ።

**የኦዲተር ማስተር ቢሮ**
ሁሉም የኦዲተር ማስተር ችሎቶች ባሁኑ ጊዜ ዌብኤክስ በመጠቀም በርቀት በመካሄድ ላይ ይገኛሉ። አካላት በአካል መቅረብ የለባቸውም። አካላት ችሎቱን በቴሌፎን ወይም በቪድዮ መሳተፍ ይኖርባቸዋል፣ ወደ ቢሮው በአካል ሪፖርት ማድረግም የለባቸውም። ችሎትን በርቀት እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ የሚያሳዩ መመሪያዎች ለሁሉም አካላት ይቀርባሉ።

ከኦገስት 1፣ 2020 ጀምሮ የወጡትን ሁሉንም ትእዛዞች ተከራካሪ አካላት ማክበር ይኖርባቸዋል። አስቀድመው ተቀጥረው የነበሩ ችሎቶችን ሌላ ቀን ቀጠሮ የሚሰጡ፣ አዳዲስ ጉዳዮችን የችሎቶች ቀን ቀጠሮ የሚሰጡ ትእዛዞችን ቢሮው በማውጣት ላይ ይገኛል።

ሁሉም ሰነዶች በሰራተኞች በርቀት ሂደት እየተደረገባቸው ይገኛል። ሁሉም ሰራተኞች ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም. እስከ 5፡00 ፒ.ኤም. ድረስ በርቀት ይገኛሉ።

ሰነዶች በኢመይል ለAuditor.Master@dcsc.gov ወይም በፖስታ ለ፡ Office of the Auditor-Master, 500 Indiana Avenue NW, Washington, DC 20001 ማስረከብ ይችላሉ። ንብነት ያላቸው ሰነዶች (ሰንሲቲቭ ዶኪመንትስ) ወደ AMFinancialBox@dcsc.gov በኢመይል መላክ ይችላሉ።

ሁሉም ችሎቶች የተደረጉባቸውና ሁሉም ሰነዶች የተረከቡባቸው ጉዳዮች በተመለከተ ሪፖርቶች በመዘጋጀት ይገኛሉ። ሪፖርቶች እንደተጠናቀቁ ለአካላት እንዲደርሱ ይደረጋል። ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎን ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-626-3280 ወይም በኢመይል በAuditor.Master@dcsc.gov ያግኙ።

**የፍትሐብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)**
የፍትሐብሔር ክፍል ለፍትሐብሔር እርምጃ (ሲቪል አክሽንስ) ጉዳዮች በሞልትሪየ ህንጻ፣ ለአነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች (ስሞል ክለይምስ) እና ለአከራይና ተከራይና (ላንድ ሎርድ ኤንድ ቴናንት) ጉዳዮች ደግሞ በህንጻ B ለህዝብ አገልግሎት ለመስጠት ክፍት ነው። የስራ ሰአታት ከሰኞ - አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም - 5፡00 ፒ.ኤም. ነው። ሰነዶች በተጨማሪ በኢፋይሊንግ (eFiling) በኩል ሂደት ሊደረግላቸው ይችላል። የዳኛ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው አስቸኳይ አቤቱታዎች (ኢመርጀንሲ ሞሽንስ) እና ከክፍያ ነጻ (ፊ ወይቨር) ማመልከቻዎች ለግምገማ ወደ ዳኛ ይላካሉ።

*ለአከራይና-ተከራይ የመከላከያ ትእዛዞች (ፕሮቴክሽን ኦርደርስ) በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ክፍያዎች*
ተከራዮች ለአከራይና-ተከራይ የመከላከያ ትእዛዞች በጥሬ ገንዘብ መክፈል ይችላሉ። በጥሬ ገንዘብ የሚደረጉ ክፍያዎች ከሰኞ እስከ አርብ በ510 4th Street, N.W. በህንጻ B በሚገኘው ፍርድ ቤት በአንደኛ ፎቅ በሚገኘው የአከራይና ተከራይ ጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) ሊደረጉ ይችላሉ።

የስም ለውጥ ማመልከቻዎችና፣ የሞት እና የልደት ምስክር ወረቀት ማሻሻያ ማመልከቻዎች ጨምሮ ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በ https://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል ማድረግ የማይችሉ ተከራካሪዎች፣ አስቀድመው ክፍያ ላለመክፈል (የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ) ማመልከቻን ሰነዶቹን ወደ Civilefilings@dcsc.gov በመላክ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻዎች በድረገጻችን https://www.dccourts.gov/services/judge-in-chambers/in-forma-pauperis-fee-waiver ይገኛሉ። ክፍያ እንዳይከፍሉ ከተወሰነ ሰነዶችን በኢፋይሊንግ እንዴት ማስረከብ እንደሚችሉ የሚያስረዳ መረጃ የጸሀፊ ቢሮ ይልክልዎታል።

የአከራይና ተከራይ ወይም የመኖሪያ ቤት ሁኔታዎች ጉዳይ ያለዎት ከሆነና ሰነዶች ወይም የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፣ ድጋፍ ለማግኘት የአከራይና ተከራይ የህግ ድጋፍ መረብን (ላንድሎርድ ቴናንት ሊጋል አሲስታንስ ኔትዎርክ) በ202-780-2575 ማግኘት ይችላሉ።

የነይበርሁድ ሊጋል ሰርቪስስ ፕሮግራም የተባለው የህግ አገልግሎቶች የሚሰጥ ፕሮግራም አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ጉዳዮች በተመለከተ የህግ መረጃ ያቀርባል። በኤን.ኤል.ኤስ.ፒ. አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ሀብት ማእከል (ስሞል ክለይምስ ሪሶርስ ሰንተር) የ24-ሰዓት የቴሌፎን መስመር (ሆትላይን) 202-849-3608 መልእክት መተው ይችላሉ።

የሸማቾች ህግ ሀብት ማእከል (ኮንሱመር ሎው ሪሶርስ ሰንተር) አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች ጉዳዮች፣ እዳ መሰብሰብ፣ የኪራይ ቀብድ ማስመለስ (ሬንት ዲፖዚት ሪካቨሪ)፣ እና ሌሎች የሸማቾች ጉዳዮች በተመለከተ መረጃ ያቀርባል። እንደነ በባንክ ሂሳብዎ የተያዘ ነገር (አታችመንት ኦፍ ባንክ አካውንት) እና አቤቱታ (ሞሽን) እና የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የመሳሰሉትን የሸማቾች ጉዳዮች ቢኖርብዎ፣ የዲ.ሲ. ባር ፕሮ ቦኖ ማእከል - የሸማቾች ህግ ሀብት ማእከል (ኮንሱመር ሎው ሪሶርስ ሰንተር) ጊዝያዊ የቴሌፎን መስመር 202-780-2574 መደወል ይችላሉ።

ቅጂዎች እና መረጃ ለመጠየቅ እባክዎን የሚመለከታቸው የጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮዎች በሚከተሉት የቴሌፎን ቁጥሮች በመደወል ወይም በክፍሉ ድረገጽ በቀኝ በኩል በሚገኝ ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) በሚል አዝራር (በተን) በመጫን ያግኙ።




*የፍትሐብሔር እርምጃ (ሲቪል ኤክሽን) ቅርንጫፍ፡*
202-879-1133
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/requesting-over-10k
ቅጂዎች ለመጠየቅ፡ CivilDocket@dcsc.gov

*የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ፡*
202-879-4879
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/landlord-tenant
ቅጂዎች ለመጠየቅ፡ L&TGroup@dcsc.gov

*አነስተኛ የይገባኛል ጥያቄዎች (ስሞል ክለይምስ) ቅርንጫፍ፡*
202-879-1120
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/requesting-10k-or-less
ቅጂዎች ለመጠየቅ፡ SmallClaimsDocket@dcsc.gov

**የወንጀል ሰለባዎች ካሳ ፕሮግራም (ክራይም ቪክቲምስ ኮምፐንሴሽን ፕሮግራም)**
ተጨማሪ ማስታወቂያ እስኪሰጥ ድረስ ለወንጀል ሰለባዎች ካሳ ፈንድ ፕሮግራም (ሲ.ቪ.ሲ.ፒ.) የሚደረጉ ማመልከቻዎች በሰራተኞች በርቀት ሂደት እየተደረገላቸው ይገኛል። አዳዲስ ማመልከቻዎች ወደ CVCPapplications@DCSC.gov በኢ-ሜይል በመላክ ወይም ከ9፡00 ኤ.ኤም. - 4፡00 ፒ.ኤም ድረስ በ515 5th Street, N.W., Washington, DC 20001 ማስረከብ ይችላሉ። ማመልከቻውን በማጠናቀቅ ረገድ እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ ወይም ማመልከቻዎ በተመለከተ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ፣ ሰራተኞች ከሰኞ እስከ አርብ ከ9፡00 ኤ.ኤም. - 4፡00 ፒ.ኤም ድረስ በቴሌፎን ቁጥር (202) 879-4216 ይገኛሉ። ማመልከቻዎች በተጨማሪ በ515 5th Street, N.W., Washington, DC 20001 ወይም በማህበረሰቡ በሚገኙ በፍርድ ቤቱ ሚዛናዊ እና መልሶ የማቋቋም የፍትህ ማዕከላት (ባላንስድ ኤንድ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ሰንተርስ) ተሞልተው ሊጣሉ ይችላሉ።

የማህበረሰብ ቦታዎቹ (ሳይትስ) የተለዩ አከባቢዎች ለማወቅ በሚቀጥለው ይጫኑ Click here።
https://www.dccourts.gov/sites/default/files/Remote-Sites-Information-Sheet.pdf

የወንጀል ሰለባዎች ካሳ ማመልከቻ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ይገኛል
https://www.dccourts.gov/sites/default/files/divisionspdfs/NEW_CVCP_Application_12.9.21_fillable.pdf

ብቁ የሆኑ የይገባኛል ጥያቄ ጠያቂዎች ምግብና የሜትሮ ካርዶች ከ515 5th Street, N.W., Washington DC 20001 ከሰኞ እስከ አርብ ከ 9:00 ኤ.ኤም. - 1:00 ፒ.ኤም. ማግኘት ይችላሉ።

**የወንጀለኛ ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)**

የፍርድ ቤት መዝገቦች እና አንዳንድ ሰነዶች በ https://eaccess.dccourts.gov/eaccess መታየት ይችላሉ። መቀጮ፣ ክፍያ ወይም ማካካሻ (ፋይን፣ ፊ አር ረስቲትዩሽን) መከፈል ከፈለጉ እባክዎ በ202-879-1840 ይደውሉ ወይም ወደ CRMPay@dcsc.gov ኢ-መይል ይላኩ።

የዋስ ገንዘብ (ቦንድ) በኦንላይን ለመክፈል እባክዎን ወደ BondPayPortal@dcsc.gov ኢ-መይል ይላኩ። የጥሬ ገንዘብ የዋስ ገንዘብ (ካሽ ቦንድ) በአካል በሞልትሪየ ኮርትሀውስ በክፍል 4003 በሚገኘው የወንጀለኛ የፋይናንስ ቢሮ (ክሪሚናል ፋይናንስ ኦፊስ) ከ9:00 ኤ.ኤም. - 4:00 ፒ.ኤም. ከሰኞ እስከ አርብ መክፈል ይችላሉ። የኦንላይን የዋስ ገንዘብ (ቦንድ) ክፍያዎች ከሰኞ - አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም. - 4:00 ፒ.ኤም. (ኢስተርን ታይም) ሂደት ይደረግላቸዋል።

የተረጋገጡ (ሰርቲፋይድ የሆኑ) ቅጂዎች ለማግኘት የሚደረጉ ጥያቄዎች በኢ-መይል በCriminalMotionSealTeam@dcsc.gov ወይም በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1362 መደረግ ይችላሉ።

በኦንላይን የሚደረግ የክሬዲት ካርድ ግብይት የ$1,000 ገደብ አለው። ማንኛውም ከስራ ሰአታት በኋላ (4፡00 ፒ.ኤ. ኢስተርን ታይም ከሰኞ - አርብ) የሚደረግ ግብይት በሚቀጥለው የስራ ቀን ሂደት ይደረግበታል።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ወይም የሰነዶች ቅጂ ለመጠየቅ እባክዎን የወንጀል ክፍል ጸሀፊ (ክለርክ) ቢሮ በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1373 ወይም በኢ-መይል CriminalCaseManagement@dcsc.gov ያግኙ።

**የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)**
በድንገተኛ አደጋ ላይ ካሉ 911 መደወል ይኖርብዎታል።

ተከራካሪ አካላት የሚከተሉትን ትእዛዞች ይሰጥዎ ዘንድ ለቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል መጠየቅ ይችላሉ፡

- የፍትሐብሔር መከላከያ ትእዛዝ (ሲ.ፒ.ኦ.)፣
- ጸረ-ማሳደድ ትእዛዝ (አንታይ-ስቶኪንግ ኦርደር) (ኤ.ኤስ.ኦ.)፣

- እጅግ በጣም አደገኛ መከላከያ ትእዛዝ (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደር) (ኢ.አር.ፒ.ኦ.)፣ ወይም
- በነዚህ ጉዳዮች ጊዝያዊ፣ ወይም አንድ አካል ብቻ በተገኘበት የሚሰጥ ትእዛዝ

እነዚህ ትእዛዞች እንዲሰጥዎ ጥያቄዎ በሚከተሉት መንገዶች ማቅረብ ይችላሉ፡

1. ዲ.ሲ. ሴፍ ክሪቲካል ሪስፖንስ ቲም (ወሳኝ ምላሽ ሰጪ ቡድን) በ(800) 407- 5048 በመደወል፣
2. በwww.probono.net/dccourts በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ፣
3. ወደ DVD@dcsc.gov ኢ.መይል በማድረግ፣ ወይም
4. በ500 Indiana Avenue, NW Room 4510 በሚገኘው ሞልትርየ ህንጻ በአካል ፋይል በማድረግ።

የፍትሐብሔር መከላከያ ትዕዛዝ አቤቱታና ቃለ መሐላ ለማግኘት በሚቀጥለው ይጫኑ Click here፣
የጸረ-ማሳደድ ትዕዛዝ አቤቱታና ቃለ መሐላ ለማግኘት በሚቀጥለው ይጫኑ Click here፣ እና
እጅግ በጣም አደገኛ መከላከያ ትእዛዝ (ኤክስትሪም ሪስክ ፕሮቴክሽን ኦርደር) አቤቱታና ቃለ መሐላ ለማግኘት በሚቀጥለው ይጫኑ Click here።
ሊሞሉ የሚችሉ (ፋይላብል) ቅጾች በዲ.ሲ. ፍርድ ቤት ድረገጽ ለማግኘት በሚቀጥለው ይጫኑ click here.

በሲ.ፒ.ኦ. ጉዳይ አካላት ስምምነት ላይ ከደረሱ የተስማሙበት የሲ.ፒ.ኦ. ስምምነት ወደ DVDhearings@dcsc.gov ኢ.መይል ማድረግ ይችላሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎና የሰነዶች ቅጂዎች ለመጠየቅ እባክዎን ቢሮውን በ202-879-0157 ያግኙ ወይም ወደ DVD@dcsc.gov ኢ.መይል ይላኩ።

**የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)**

የቤተሰብ ፍርድ ቤት ህዝብ የሚገለገልባቸው ቢሮዎች (ማእከላዊ መቀበያ ማእከል (ሰንትራል ኢንቴክ ሰንተር)፣ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች (ዶመስቲክ ሪሌሽንስ)፣ ወላጅነትና ድጋፍ፣ ወጣት ጥፋተኛ እና ቸልተኝነት (ጁቨናይል ኤንድ ኔግለክት)፣ እና የጋብቻ ቢሮ ጨምሮ) በአካል አገልግሎት ለመስጠት ክፍት ናቸው። የቤተሰብ ፍርድ ቤት በተጨማሪ በኢፋይሊንግ (eFiling) በኩል የተላኩ ሰነዶች ሂደት በማድረግ ይገኛል። አስቸኳይ አቤቱታዎች ለግምገማ ወደ ተመደበው ዳኛ ይላካሉ፣ አብዛኛዎቹ ችሎቶች በርቀት ይካሄዳሉ። እባክዎን ሁሉም አስቸኳይ ጉዳዮች፣ ከበአላት በስተቀር፣ ከሰኞ እስከ አርብ ባሉ ቀናት ከ4፡00 ፒ.ኤም. በፊት ፋይል መደረግ እንደሚኖርባቸው ይገንዘቡ።

ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በ https://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከልን (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ ሄልፕ ሰንተር) ከሰኞ - አርብ ከ8፡00 ኤ.ኤም. - 5፡00 ፒ.ኤም. በአካልና በርቀት አገልግሎት ለመስጠት ክፍት ነው። ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ እርዳታ የሚፈልጉ ተከራካሪዎች የቤተሰብ ፍርድ ቤት ራስ-አግዝ ማእከልን (ፋሚሊ ኮርት ሰልፍ ሄልፕ ሰንተር) በ202-879-0096 ያግኙ ወይም የሞልትርየ ኮርትሀውስ ክፍል ቁጥር JM-540 ይጎብኙ።

የሰነዶች ቅጂዎች ቢፈልጉ እባክዎን ወደ FamilyCourtCertifiedCopies@dcsc.gov ኢ.መይል ያድርጉ። ለማናቸውም ሌሎች ጥያቄዎች ቢኖርብዎ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የጥሪ ማእከል (ፋሚሊ ኮርት ኮል ሰንተር) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1212 ያግኙ።

*የጋብቻ ቢሮ*

የጋብቻ ቢሮ የጋብቻ ፈቃዶች (መርየጅ ላይሰንስስ) ማመልከቻዎች በአካልና በርቀት ሂደት በማድረግ ይገኛል፣ ጋብቻም በቪድዮ ኮንፈረንስ እያካሄደ ይገኛል። ሁሉም አካላት - ሁለቱም ተጋቢ አካላትና ጋብቻውን የሚያካሂደው ሰው- ስነ ስርአቱ በሚደረግበት ጊዜ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በአካል ያሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

የማመልከቻ ሂደቱ ለመጀመር በ https://www.dccourts.gov/form/marriage-application የሚገኘው ምናባዊ (የኦንላይን) ማመልከቻው አጠናቅቀው ያስረክቡ። ማመልከቻው ለማጠናቀቅና ለማስረከብ ኮምፒውተር ወይም ሞባይል መሳሪያ (አይፓድ፣ ታብሌት ወይም ስማርትፎን) መጠቀም ይችላሉ። የማመልከቻው ሂደቱ ለመጨረስ የጋብቻ ቢሮ ተወካይ ያገኝዎታል። ምንም እንኳን የጋብቻ ፈቃዱ (ሜርየጅ ላይሰንስ) በአካል መጥተው ለመውሰድ እቅድ ቢኖርብዎም በኦንላይን የሚደረገውን ማመልከቻ እንዲያስረክቡ በጣሙን ይበረታታሉ። በምናብ (ኦንላይን) ማመልከት የማይችሉ ከሆነ ማመልከቻውን በአካል መሙላት ይችላሉ።

የጋብቻ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ ቅጂ (ሰርቲፋይድ ካፒ) ቢፈልጉ፣ እባክዎን ይህን ቅጽ ይሙሉ፡ https://www.dccourts.gov/webform/marriage_certified_copy/። በዚህ ሂደት ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን ወደ 202-879-1212 ይደውሉ። በተጨማሪ ምስክር ወረቀቱ በአካል እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ።

**የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማህበራዊ አገልግሎት ክፍል (ፋሚሊ ኮርት ሶሻል ሰርቪስስ ዲቪዥን)- ሲ.ኤስ.ኤስ.ዲ.**
የቤተሰብ ፍርድ ቤት ማህበራዊ አገልግሎት ክፍል (ፋሚሊ ኮርት ሶሻል ሰርቪስስ ዲቪዥን) (ሲ.ኤስ.ኤስ.ዲ.) የወጣት ጥፋተኞች አገልግሎቶች ምዝገባ ቢሮ (ኢንቴክ ጁቨናይል ሰርቪስስ) በ1000 Mount Olivet Rd., NE በሚገኘው የወጣት አገልግሎቶች ማእከል (ዩዝ ሰርቪስስ ሰንተር) (ዋይ.ኤስ.ሲ.) በቀን 24 ሰአታት፣ በ3 የግዳጅ ፈረቃዎች፣ በሳምንት 7 ቀናት መስራቱ ይቀጥላል። የልጅ መመሪያ ክሊኒክ (ቻይልድ ጋይዳንስ ክሊኒክ) (ሲ.ጂ.ሲ.) በዋይ.ኤስ.ሲ. ተጠልለው ላሉ ወጣቶች በቦታው ስነልቦናዊ ምዘናዎች (ሳይኮሎጂካል ኢቫሉኤሽን) መስጠቱ ይቀጥላል። ወደ መጠለያ ቤቶች የተመለሱ ወጣቶች ጨምሮ በማህበረሰብ መቼት የሚኖሩ ወጣቶች እንደየ ሁኔታቸው በድንገተኛ ደረጃ ብቻ ቀጠሮ ይሰጣቸዋል። በቀነሰ የጊዜ ሰሌዳ በኩል በጁን 27፣ 2021 ዳግም የጀመረው እና በዲሰምበር 21፣ 2021 ለጊዜው የታገደው በተመጣጠነና አዳሽ ፍትህ (ባላንስድ ኤንድ ረስቶሬቲቭ ጀስቲስ) (ቢ.ኤ.አር.ጀይ.) የመጣያ ማእከሎች (ድራፕ ኢን ሰንተርስ) ይቀርቡ የነበሩ የክትትል አገልግሎቶች (ሱፐርቪዥን ሰርቪስስ) ጊዚያዊ እገዳውን ማንሳት ያለበት አዋጪነት ለመወሰን በጃንዋሪ 5፣ 2022 ዳግም-ግምገማ ይካሄድበታል። በምሽትና በሳምንት መጨረሻ በቦታው በቢ.ኤ.አር.ጀይ. ይሰጡ የነበሩ አገልግሎቶችና ፕሮግራሞች በምናብ (ቨርችዋሊ) ወይም የ6 ጫማ ማህበራዊ ርቀትን በመጠበቅ በአካል ይካሄዳሉ። ወጣቶች በሰአት እላፊ ማረጋገጥና በሲ.ኤስ.ኤስ.ዲ. ፕሮቤሽን ኦፊሰሮች (ፒ.ኦ.) እና ኮንትራክት አማካሪዎች (መንተርስ) በጋራ በሚያቀላጥፉት ምናባዊ ቡድኖች (ቨርችዋል ግሩፕስ) ይሳተፋሉ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ ወጣቶች፣ ቤተሰቦች እና ባለ ድርሻ አካላት ወደ 202-508-1800 መደወል ይችላሉ ወይም ወደ Kathie.Gant@dcsc.gov ወይም Sharon.Proctor@dcsc.gov ኢ-መይል መላክ ይችላሉ።

## የጁሮሮች ቢሮ (ጁሮርስ ኦፊስ)

ጁሮሮች በምናብ (ኦንላይን) በ www.dccourts.gov/jurorservices በኩል የጁሮሮች መጠይቅ ማጠናቀቅ፣ የጁሪ ግዴታ አገልግሎት ማስተላለፍ፣ እና ከጁሪ ግዴታ አገልግሎት እንዲተዉ መጠየቅ ይችላሉ። ጁሮሮች በተጨማሪ የተጠናቀቀ መጠይቃቸው ወይም የተጠናቀቀ መጠይቃቸው ምስልን ለ jurorhelp@dcsc.gov በኢ-መይል መላክ ይችላሉ።




የጁሮር ቢሮ፣ በቴሌፎን በ202-879-4604፣ በኢ-መይል በ jurorhelp@dcsc.gov ወይም በድረገጹ https://www.dccourts.gov/jurors/about-your-jury-duty በቀኝ በኩል በሚገኘው ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) የሚለውን አዝራር (በተን) በመጫን፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም. -
5:00 ፒ.ኤም. ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ነው።

## የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን)

የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) በአካልና በኢፋይሊንግ (eFiling) በኩል ሰነዶች በመቀበል ይገኛል።

አስቸኳይ ጉዳዮች (21-ቀን እና ጊዜያዊ ሞግዚትነት) ለግምገማ ወደ ዳኛ እየተላኩ ነው፣ ሁሉም ችሎቶች በርቀት እየተካሄዱ ነው። በተጨማሪ፣ ችሎት ለማያስፈልጋቸው አስቸኳይ-ላልሆኑ ጉዳዮች ዳኞች ውሳኔ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

የ21-ቀናት ጊዝያዊ የሞግዚት ማመልከቻ ፋይል ለማድረግ ሰነዱን ወደ ProbateEmergencyFilings@dcsc.gov ኢሜይል ያድርጉ።

አዲስ የ90-ቀናት የጤና እንክብካቤ ሞግዚት ወይም ማመልከቻ ለአጠቃላይ የፍርድ ቤት ሂደት ፋይል ማድረግ ቢፈልጉ ማመልከቻው ወደ probatefilings@dcsc.gov ኢሜይል ያድርጉ። የመዝገብ ቁጥር ያለዎት ከሆነ ማመልከቻው በኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ፋይል መደረግ ይኖርበታል።

አስቀድሞ መከፈል ያለባቸው ክፍያዎች እንዳይከፍሉ መጠየቅ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎን በድረገጻችን በhttps://www.dccourts.gov/services/judge-in-chambers/in-forma-pauperis-fee-waiver የሚገኘውን የክፍያ ነጻ አድርጉልኝ ማመልከቻን ይሙሉ።

ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በ https://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

ለተጨማሪ መረጃና ለሌላ የኑዛዜ ማረጋገጫ በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) ድረገጽ https://www.dccourts.gov/services/probate-matters ይመልከቱ።

የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍልን (ፕሮቤት ዲቪዥን) ከቴሌፎን ቁጥሮቻቸው ባንዱ ቁጥር በመደወል፣ ኢሜይል በመላክ፣ ወይም በክፍሉ ድረገጽ በቀኝ በኩል በሚገኘው ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) የሚለውን አዝራር (በተን) በመጫን ማግኘት ይቻላል።




አጠቃላይ የኑዛዜ ማረጋገጫ (ፕሮቤት) ጥያቄዎች
ቴሌፎን፡ 202-879-9460
ኢመይል፡ Probateinquiries@dcsc.gov
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/probate-matters

የኑዛዜ ማረጋገጫ በመሙላት ረገድ ድጋፍ የሚፈልጉ ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች የኑዛዜ ማረጋገጫ ክፍልን (ፕሮቤት ዲቪዥን) ራስ-አግዝ ማእከል (ሰልፍ ሄልፕ ሰንተር) በProbateSelfHelpCenter@dcsc.gov ማግኘት ይችላሉ።

**የግብር ክፍል (ታክስ ዲቪዥን)**
ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በ https://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ። ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በአካል ፋይል ማድረግ ይችላሉ፣ ወይም ማመልከቻዎቻቸው (ፕሊዲንግስ) ወይም የማመልከቻዎቻቸው (ፕሊዲንግስ) ምስል በኢመይል አድራሻ TaxDocket@dcsc.gov በመላክ፣ ፋይል ማድረግያ ክፍያቸው ደግሞ በቼክ ወይም ማኒ አርደር አዘጋጅተው ለD.C. Superior Court, Tax Division, 500 Indiana Ave., NW, Suite 4100, Washington, DC 20001 መላክ ይችላሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ይግብር  ክፍልን (ታክስ ዲቪዥን) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1737 ወይም በኢመይል TaxDocket@dcsc.gov ያግኙ።

*በተጨማሪ፣ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ለሱፒርየር ፍርድ ቤት ጸሀፊ (ክለርክ) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1400 ማግኘት ይችላሉ።*